# ክልል አይበጅም ለከብትም!



ሕዝብን እንደ ላም ቆጥረህ፣ በክልል በረት የምታልብ!
እንደ አውሬ ደመነፍስ ሳይሆን፣ እንደ ሰው አንጎል ተጠቀም፤
ክልል እንኳን ለሰው ልጅ፣ ለዶሮ ለከብት አይበጅም፡፡

በክልል ሰይጣን ደቁነው፣ የሚሉት ቁማር ተጫወትን፤
ምራቁን ውጦ ዝም ቢል፣ ቢታገስ ቢሆን ኢዮብን፣
ክልልህ ግባ እያሉ፣ በሜንጫ አረዱት አማራን፡፡

አማራ ነፃ ሕዝብ እንጅ፣ የእንሰሳ መንጋ አይደለም፤
እንደ ከበት በክልል ታስሮ፣ ሳር ቅጠል ሲነጭ አይኖርም፡፡

አማራ እንደ አንበሶቹ፣ እንደ አያቶቹ በርትቶ፤
በመላ እርስቱ ይኖራል፣ ሰው አራጅ አውሬን ድል ነስቶ፡፡

የመላ ጦቢያ አፈሩ፣ ውሀው አየሩ ይመርመር፤
በአማራዎች ሥጋ ደም፣ በአጥንቶቻቸውም ተከብሯል፡፡

ዘሩን ሊያጠፉ ቢጥሩ፤ የተንኮል ቁማር ቢሰሩም፣
አማራና ጢስ መውጫ በር፣ ጎዳናው ጠፍቶት አያውቅም፡፡

ለይህ አድግ ተንኮል ገብረህ፣ የአማራ ክልል የምትል፤
እንደ ብአዴን ካድሬዎች፣ የምትሸጥ ያያትህን ክብር፤
በታረደችው እርጉዝ ግማዴ፣ ልሳን ጉረሮህ ይታሰር፡፡

እንደ ክልል አምላኪ ጪራቆች፣ ፅንስን ተናቱ አያርድም፤
እንደ ጋማ ከብት ተነድቶ፣ እንደ አውሬ እሬሳ ጎትቶ አያውቅም፤

አማራ ሰፊ አገር እንጅ፣ ክልል ከልሎት አይኖርም፡፡

ክልል ፌደራል የምትል፣ ሕዝብ ልታፋጅ አሁንም፣
እባክህ በእግርህ ቆመህ ሂድ፣ ዝንጀሮ አትሁን ዘላለም፣
እንኳን እዝለ ልቡና ላለው ሰው፣ ክልል አይበጅም ለከብትም!

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
ታህሳስ ሁለት ሺ አስራ ሶስት ዓ.ም.